# የደምቢዶሎ ተማሪዎችን እገታ በትመለከተ እስካሁን የተደረሰባቸዉ እውነቶች

ደምቢ ደሎ ዩኒቨርሲቲ በኅዳር ወር ገደማ በዩኒቨርሲቲዎች ግጭት ከተስተዋለባቸው ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ነበር፡፡

- በዚህም የፌዴራል መንግሥቱ እና የክልሉ የጸጥታ አካላት ዩኒቨርሲቲውን የመጠበቅና የማረጋጋት ሥራ እንዲሠሩ ፌዴራል ፖሊስም ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረው ተደርጓል፤
- በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ግቢውን ለቀው ወደ ቤተሰቦቻቸው መሄድ ሲጀምሩ የአካባቢው ኅብረተሰብ እና የጸጥታ መዋቅሩ ተማሪዎቹ እንዳይሄዱ በማግባባትም ወደ ግቢ ሲመልሱ ነበር፡፡
- በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎቹ ወደ ጋምቤላ አቅንተው በመጓዝ ላይ እያሉ የአካባቢውን አንድ አመራር ፣ የ 2ኛ ደረጃ ትምርት ቤት ተማሪዎች፣ ወጣቶች እና ልዩ ልዩ ነዋሪዎች እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአንፊሎ ወረዳ ሱዲ በተባለ ቦታ ኅዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም ታግተው የነበሩ መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡
- የተማሪዎች መታገት ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ የመከላከያ ሠራዊት እና ሌሎች የጸጥታ አካላት ባደረጉት አሰሳ 21 ተማሪዎችና ተጨማሪ የአካባቢው ነዋሪዎች ተለቀው ነበር፡፡
- ተማሪዎቹን የአካባቢው አመራሮች ደምቢደሎ ዩኒቨርሲቲ ግቢ እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡ ይህም ጥር 2 ቀን 2012 ዓ.ም ከሰሡነው መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ከትናንት በስቲያ የፌዴራልና ክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በቦታው ተገኝተን ባደረገው ውይይትና ግምገማ ያረጋገጥነው ነው፤
- ሠራዊቱ ወደ ግቢ ከመለሳቸው በኋላ ከእነርሱ በተጨማሪ ወደ 800 ተማሪዎች በተለያዩ አማራጭ ግቢውን ለቀው ወጥተዋል።
- እስከ አሁንም ወደ ግቢ ተመልሰው ትምህርት አልጀመሩም፡፡
- ይህ በእንዲህ እንዳለ ቀሪ ተማሪዎች ታግተዋል የሚል መረጃ ከተገኘ በኋላ የጸጥታው መዋቅር ፣የአካባቢው አመራር እና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ የማጣራት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡
- በሌላ በኩል አንድ ከአባቷ ጋር ስትጓዝ የነበረች የአካባቢው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እና ሌሎች አምስት ወጣቶች የተያዙ መሆኑን ዘግይቶ ጥቆማው ደርሶ እየተጣራና ሥራ እየተሠራበት ይገኛል፤
- እነዚህን መረጃዎች በመያዝ መረጃ የማጣራት እና ተማሪዎቹን የማፈላለግ ተግባራት በተለያዩ አካላት ሲከናወኑ ቆይተዋል።

- በተለያዩ መንገዶች እንደጠፉ የተገለጡ 17 ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሆን አለመሆናቸውን ከዩኒቨርሲቲው የመረጃ ማዕከል እና ከአገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ሲጣራ ዩኒቨርሲው ከ17ቱ ተማሪዎች 12ቱ በዩኒቨርሲቲው ተመድበው በመማር ላይ የነበሩ መሆናቸውን ያረጋገጠ ሲሆን ቀሪዎቹ አምስቱ በዩኒቨርሲቲ ስማቸው አልተገኘም፡፡
- አጠቃላይ ስማቸው በሚዲያም ያልተገለጠ ነገር ግን ወላጆች ልጆቻችን ጠፍተዋል ያሏቸው ሁለት ተጨማሪ ተማሪዎች በመገኘታቸውና ከዩኒቨርሲቲው ሲጣራ እነዚህ ሁለቱ ተማሪዎችን ጨምሮ በተለያየ መልኩ ከተገለጹት 19 ተማሪዎች ውስጥ 14ቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሲሆኑ አምስቱ ግን የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አለመሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡
- እስከ አሁን ድረስ በልዩ ልዩ መልክ እንደጠፉ የተገለጸው የተማሪዎች ቁጥር 19 ሲሆን ልጆቻችን ወደ እኛ አልመጡም፣ ጠፍተውብናል ብለው ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ያቀረቡት ወላጆች ቁጥር 11 ሲሆን በተለያየ መልኩ ጠፍተዋል ተብለው ከተገለፁት ተማሪዎች ውስጥ 9ኙ ወላጆቻቸው ሪፖርት አላደረጉም ወይም የወላጆቻቸውን አድራሻ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

**በመንግሥት በኩል**

- መረጃው ከደረሰ ጀምሮ በፌዴራል እና በክልል የጸጥታ መዋቅር ጥምረት መረጃ የማሳሰብና ተማሪዎቹን ዜጎችን የማፈላለግ ሥራ በመሠራት ላይ ነው
- አንድ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሥራውን እየገመገመና እየመራ ነው። ካሁን ቀደም ሁለት ጊዜ ሁኔታውን የሚያጣራ ቡድን ተልኮ ሪፖርት አቅርቧል። በቅርቡም ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ከሰላም ሚር፣ከጸጥታ ተቋማት፣ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚር፣ ያሉበት ቡድን ወደ ደምቢዶሎ ተንቀሳቅሶ በአካባቢው የሚገኘው የፀጥታ መዋቅር አካባቢው አመራሮች ፣ተማሪዎችና ልዩ ልዩ አካላት ጋር ግምገማ አካሂዷል ጠቃሚ መረጃና ማስረጃዎችን ማግኘት ችሏል፡፡
- ልኡኩ ባሰባሰበው መረጃና ግምገማ መሠረት ጠንካራ የምርመራ እየተሠራ ነው፡፡

//